# በርጬማ ለማኙና የበርጬማው ጌታ!!

ከአሊ ሁሴን



## በርጬማ ለማኙ * * *

እነሆ አምጥተናል፣
እኛን ለበረከት፣
መለስ እግዚእነ ተሳሃለነ
እምልብከ እሩህቅ
ወብዙሃ ምህረት፣
ያደረግነው ስህተት፣
ቢኖርም በፊርማ፣
ያ! ሁሉ ተከድኖ
ካገኘን በርጬማ!
ደም እንደ ቀይ ቀለም
ብናይ እንኳ ፊሶ፣
ሰው ሞተ ታሰረ
እየዬና ለቅሶ፣
እርመ በላ ይበሉን፣
አይኖርም ጨርሶ፣
የአሜሪካ ጠንቋይ፣
አዋቂ ጠይቀን፣
እጣ ክፍላችንን፣
ዘርዝሮ ሲነግረን፣
እርስዎ ከዙፋንዎ፣
እኛ ከበርጬማ፣
ምክር ሲለግሰን፣
በዚህ እንድንስማማ!
ከእግርዎ ስር መቀመጥ፣
ይጠቅማል ማለቱ፣
ገረመን ደነቀን፣
የፈረንጅ ብልጠቱ፣
በእሱ መጀን ይሁን፣
እርስዎን በባረከ፣
እንኳንስ በርጬማ፣
ከገነት ይገባል በነጪ ያመለከ!!
በርጬማም ከጠፋ፣
ከዚያም ዝቅ ብለን፣
ወርደን ከጫማ ስር፣
እግዳሚው ይምጣልን፣
ምንም አይለንም ቅር!
ይህም ካልተሳካ፣
ይሰራልን መደብ፣
በተፈራረምነው!
መመሪያና ህገ-ደንብ፣
ሰጥ ለጥ ብለን፣
እንተኛለን በአደብ!!!

## የበርጩማ ጌታ * * *



አረ ቀና በሉ፣
በርጩማው አያልቅም፣
ከእናንተ በሁዋላ ነጣቂ ካልመጣ፣
የለም የሚለቅም፣
እኛን ሀፍረት ዋጠን፣
በእናንተ መነጠፍ፣
በቃ አታጎንብሱ፣
ምቀኛችን ይርገፍ !
የሚተላለፍ ነው፣
ለልጅ ልጆቻችሁ፣
ታሪክ ሰርታችሁዋል፣
በደም ፈርማችሁ፣
ቅንጅቱ ቀርቶ፣
ቅን አንጀት ሆናችሁ፣
ለወግ ለማዕረግ፣
ስለ ደረሳችሁ፣
ዕድሜ ለበርጩማው፣
እንኳን ደስ ያላችሁ!
ለታዳሚዎቻችሁ፣
በውጪ አለም ላሉ፣
ፍጥምጥማችንን፣
ከጠላት አደጋ እንዲከላከሉ፣
በየፓልቶኩ ውስጥ፣
ወጥረው እንዲሰሩ፣
ዋስትና ስጧቸው፣
ጭራሽ እንዳይፈሩ፣
ለበርጩማ ብለን፣ ዛሬ ብንሳሳም፣
ያለፈውን ጊዜ፣ በፍፁም አንረሳም!
ብላችሁ ለፍፉ፣
ለጥላ ከለላ፣
ጠላታችን ይክሰም፣
አፈር ድቤ ይብላ!
እንጠብቃለን በናፍቆት ሰቀቀን፣
ኮርማ ሰንጋ ልንጥል፣ የሰርጋችንን ቀን፣
እስከዚያው ድረስ ግን፣
ይብቃ ማጎንበሱ፣
በክፉ የሚያዩን፣
ይቃጠሉ ይጢሱ!